የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

# አባቴ በአለንጋ ገርፏችኃል፥ እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ

---

በዩ.ኤስ. አሜሪካ የፖለቲካ ስልጣን ታሪክ ውስጥ እንደኖሩበት ዘመን ተፅዕኗቸው ቢለያየም የሩዝቬልት፣የኬኔዲ አልያም የቡሽ ቤተሰቦች በመጀመሪያው ረድፍ የሚገኙ ተፅዕኖ ፈጣሪ እና በአለም ፖለቲካ ላይ አሻራቸውን ያኖሩ ሊባል ይችላል። ይሁን እንጂ ገና በ19ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ  የአሜሪካ ካፒታሊታዊ ስርዓት ከድንበሩ ተሻግሮ ወደ እነ ሀዋይ ደሴት መፍሰስ ሲጀምር ፥ ብሎም እየጠቀለለ የራሱ አካል ማድረግ ሲጀምር በካፒታሊስቱ እና በፖለቲከኛው መካከል የጥቅም መስተጋብርን የሚፈጥር አካል ተነሳ። ይህም በመጀመሪያ የአሜሪካንን በኋላም የአለምን ፖለቲካ ከካፒታሊስቱ ጥቅም አንፃር የሚቃኝ በተለምዶ ''ኮርፖራቶክራሲ'' የሚባለውን አስተሳሰብ የፈጠረ አካል ነው። በዚህ ረገድ ከላይ ካየናቸው ቤተሰቦች ይልቅ በአለማችን ከተከሰቱ ሁለት የአለም ጦርነቶች ጀምሮ በነበሩ ትላልቅ ሁነቶች ላይ በመሳተፍ ብሎም አንደኛው ስምንት ሌላኛው ሰባት የአሜሪካን ፕሬዝደንቶችን በማገልገል የደለስ ቤተሰቦችን የሚስተካከል የለም። በፕሬዝደንት አይዘንአወር የስልጣን ዘመንም እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች ከፍተኛውን የፖለቲካ ስልጣን ሲቆናጠጡ፤ ታላቅየው ጆን ፎስተር ደለስ ልክ እንደ አያቱ /32ኛው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር/ አልያም ልክ እንደ አጎቱ /42ኛው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር/ እሱም 52ኛው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ሆኖ ሲሾም ታናሽ ወንድሙ ኤለን ደለስ የሲ.አይ.ኤ ዳይሬክተር ሆኖ ተሾመ።ዛሬ ወደ ዋሽንግተን የሚበር ሁሉ ''የደለስ አለማቀፍ አውሮፕላን ጣቢያን'' የማየት ዕድል አለው። ያም ግዙፍ የአውሮፕላን ጣቢያ ስያሜውን ያገኘው ጆን ፎስተር ደለስን ለማሰብ በሚል በጆን. ኤፍ. ኬኔዲ ዘመን የተሰየመ ነው። በሌላ በኩል  በእስከዛሬው የሲ.አይ.ኤ. ታሪክም እንዲሁ ለስምንት ተከታታይ አመታት ሲ.አይ.ኤን በመምራት ኤለን ደለስ ብቸኛው ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ግን በዚህ የአይዘንአወር ዘመን እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች አንደኛው በገሃድ የሚታየውን መንግስት፥ ሌላኛው የስውር መንግስቱን በመምራት ኮርፖሮቶክራሲ ስጋና ደም ለብሶ በአደባባይ እንዲሄድ አድርገዋል። በተለይ

ሁለቱም ''Sullivan and Cromwell'' የሚባል በግል ለተያዙ ግዙፍ ድንበር ዘለል የንግድ ድርጅቶች /ኮርፖሬቶች/ የህግ ሽፋን የሚሰጥ ድርጅት ባለድርሻ ከመሆናቸው አንፃር የእነዚህ ግዙፍ ድንበር ዘለል የግል የንግድ ተቋማት በሌላ ሉዓላዊ ሀገር ውስጥ ያላቸው ጥቅም /በተለይ ከመሬትና ተፈጥሮ ሀብት ጋር በተያያዘ/ ሲነካ እነዚህ ወንድማማቾች የገሃዱን እና የስውሩን የአሜሪካ መንግስት እጅ በመጠቀም በኢራን የመሃመድ ሞሳድግ መንግስትን፣ በጓቲማላ የጃኮቦ አርቤንዝ መንግስትን በመፈንቅለ መንግስት ሲያስወግዱ፣ የኮንጎው ፓትሪስ ልሙምባን አስገድለዋል እንዲሁም በኪዩባው ፊደል ካስትሮ ላይ ያልተሳካን ወረራ ለማድረግ ሞክረዋል። ለዚህ ሁሉ ጣልቃ ገብነት ግን እንደሽፋን ይሰጥ የነበረው ''እነዚህ ሰዎች ኮሚኒስት ናቸው'' የሚል የሀሰት ክስ ነበር።

ከዚያም ጊዜ ወዲህ ቢሆን እነዚህ በአሜሪካና በአውሮፓ የሚገኙ ድንበር ዘለል ግዙፍ የንግድ ተቋማት በሶስተኛው ዓለም የሚገኙ ደሃ ሀገራትን የተፈጥሮ ሀብትና መሬት  በሙስናና ኃላፊነት በማይሰማቸው ባለስልጣናት ምክንያት በቀላሉ ያገኛሉ። ይሁን እንጂ በነዚህ ሀገራት ውስጥ የለውጥ ሀይል ሲመጣ እነዚሁ ግዝፍ ኮርፖሬቶች አሁን ባለው አሰራር የፖለቲኮ-ኮሜርሻል የሎቢ ድርጅቶችን በመጠቀም በነዚህ ደሃ ሀገራት ውስጥ የተነሳውን የለውጥ ፍላጎት እንዲደፈቅ ሲያደርጉ የለውጡ መሪ የሆኑትን ግለሰቦችንም እንዲወገዱ ይደረጋል። ይህንን ሁሉ አልፎ እንኳን የለውጥ እንቅስቃሴው ቢሳካ ባላቸው ትልቅ ተፅዕኖ ምክንያት ለውጡ የታሰበውን ያህል ፍሬ እንዳያፈራ ያመክኑታል። ለዚህም ዙምባብዌ አይነተኛ ማሳያ ናት።

በመሆኑም በኢንቨስትመንት ስም የሚመጡ እነዚህ አለማቀፍ ቁመና ያላቸው ድርጅቶች በተለይ መሬትና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉት ስምምነት በጥንቃቄ ካልታየ ለአንድ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለቀጣይም ትውልድ የሚተርፍ ዳፋ ይዞ ሊመጣ ይችላል። በተለይም የጥራጥሬ እና የቅባት እህሎች ዋጋ በዓለም ገበያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ መምጣት ለዚሁም በዋናነት የገበያውን ዋጋ የአቅርቦትና ፍላጎት መመጣጠን ብቻ የሚወስኑት ሳይሆን በፋይናንስ ገበያው ውስጥ አስቀድሞ በጎልድ ማን ዛክስ የተጀመረው ''ጎልድ ማን ዛክስ ኮሞዲቲ ኢንዴክስ'' በሚል ጥቅል /ፓኬጅ/ የተዘረጋው አዲሱ የፊውቸውር ማርኬት ሥርዓት በስፋት በፋይናንስ ገበያ ውስጥ መዘርጋቱ የጥራጥሬ እና የቅባት እህል ውጤቶችን ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲያሻቅብ ሲያደርገው ከገልፍ ሀገራት ሼህዎች እስከ ቻይና የመንግስት ኮርፖሬሽኖች፣ ከዎል ስትሪት ስፔኩሌተሮች እስከ ራሽያ ኦሊጋርኮች፣ ከህንድ ባለሀብቶች

እስከ ሙሰኛ የአፍሪካ መሪዎች ሁሉም በአንድነት በመሬት ቅርምት እና ወረራ ላይ እንዲሰማሩ ምክንያት ሆነ።

ለዚህም የጅምላ የመሬት ቅርምት ቀዳሚ ተጠቂ የሆኑት አንድም በሙስና እጅግ የላሸቀ አስተዳደር ያላቸው ሀገራት አልያም በተለየ ሁኔታ በውስጣዊ ቅኝ አገዛዝ የምትተዳደረው የወያኔ ትግሬዋ ኢትዮጵያ ናት።እንዲያውም አሁን አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የመሬት ወረራ መልኩን በተወሰነ ደረጃ በመቀየር ትግሬዎች አንድ ወረዳ የሚያክል መሬት ይወስዱና ከውጭ ሀገር ኢንቨስተር በደላሎች በኩል በማፈላለግ የንግድ ሽሪክ አድርገው ያመጧቸዋል። በሂደትም የሽርክና ድርሻቸውን ከግማሽ በላይ በመሸጥ በእነዚህ አለማቀፍ ድርጅቶች ጉያ በመጠለል እስከ 99 ዓመት የሚደርስ ዋስትናን ያገኛሉ። እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ እነዚህ መሬት የሚቀራመቱ ድንበር ዘለል ድርጅቶች ምንጫቸው ኤዥያም ይሁን አውሮፓ አልያም አሜሪካ በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ አሜሪካን ሀገር ካሉ ትላልቅ የፋይናንስ ተቋማት ጋር እጅግ የተሳሰረ የጥቅም ቁርኝት አላቸው። ለምሳሌ በጋምቤላ ውስጥ ቤልጅየምን የሚያክል ቦታ የወሰደው የህንዱ ካራቱሪ ካምፓኒ አሜሪካን ሀገር ቤተስዳ እና ቦስተን ከሚገኙ የኢኩቲ ኢንቨስተር /Equity Investors/ ከሆኑት ማንሱን ካፒታል እና ሳንድስቶን ካፒታል ጋር ቁርኝት አለው። ይህም ሀገሪቱ እንደሀገር የመቀጠል ዕድል አላት ተብሎ በጠበበ ዕድል ቢታሰብ እንኳን ነገ እንደጓቲማላው ጃኮቦ አርቤንዝ አይነት ሰው ተነስቶ የተፈፀመውን የመሬት ወረራ እቀለብሳለሁ አልያም አሻሽላለሁ ቢል አንድም የአርቤንዝ አልያም የዙምባብዌ ዕጣ እንደሚገጥመው ለመተንበይ ነብይ መሆንን አይጠይቅም።

ይህንን ሁሉ እንድናነሳ ግድ ያለን ከሰሞኑ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ድረ-ገጽ ላይ የወጣውን ነገር ስንመለከት በወያኔ ትግሬ የተከፈተብን ዘርፈ ብዙ ጦርነት አሁንም በአማራዊ ምድራችን ላይ በስፋት እንደቀጠለ ስለታዘብን ያንን አስመልክቶ የጋራ ግንዛቤ ይኖረን ዘንድ ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ተገደድን። መልካም ንባብ!

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሚባለው መስሪያ ቤት በድረ ገጹ ላይ የውጭ ሀገር ድርጅቶችን በሽርክና ለማስገባት የሚፈልጉ ድርጅቶች ብሎ የስምንት ድርጅቶችን ስም ዝርዝር አውጥቷል። ከነዚህ ውስጥ አራቱ በአሁኑ አጠራር የአማራ ክልል በሚባለው ምድራችን ላይ የሚገኙ ናቸው። ከነዚህ አራቱ ውስጥ አክስዮን ለህዝብ በመሸጥ የተቋቋመው የህብር ስኳር አንዱ ሲሆን ቀሪ ሶስቱ የትግሬ ድርጅቶች ናቸው። ስማቸውም:- ፍቅር ምስግና ገ/አብ ኃ/የተ/የግል ድርጅት /በአማራ ክልል ደብረብርሃን ዙሪያ ልዩ ቦታው ጠባሴ በሚባል ስፍራ/

፣ ጴጥሮስ ህዝቅኤል የወረቀት እና ወረቀት ውጤቶች ፋብሪካ /በአማራ ክልል ደብረ ብርሃን ዙሪያ። በዚህ አጋጣሚ ይህ ድርጅት ከሰል ከቻይና ካምፓኒ ጋር እንዲሁ በኦሮሚያ ክልል በማምረት የሚታወቅ ሲሆን ደን በማውደም ቁጥር አንድ ከሚባሉ የትግሬ ድርጅቶች አንዱ ነው/ እንዲሁም የስብሐት ነጋ ሶስተኛ ልጅ /በእርግጥ የስብሐት ነጋ ልጆች የንግድ ኢምፓየር ከአዲስ አበባው ''ኤኪሊ ክርኤቲቭ'' እስከ ቻይና ብሎም አውስትራሊያና ሆንግኮንግ እንዲሁም ለንደን ይዘረጋል/ በሆነችው ህያብ ስም የተሰየመውና አንድ ሺህ ሄክታር መሬት በጎጃም አዊ ዞን ጃዊ ወረዳ በመውሰድ እንዲሁም ሰባ አምስት ሚሊየን ብር የመነሻ ካፒታል ያስመዘገበ ህያብ የግብርና ኢንደስትሪ በመባል የሚታወቅ ድርጅት ነው።

በግልጽ እንደሚታወቀው ግን ብዙም ያልተጮኸለት አንድ ነባራዊ ሀቅ ቢኖር ከጋምቤላ ቀጥሎ ከፍተኛ የሆነ የመሬት ቅርምት የተፈፀመበት ቦታ ቢኖር የአማራ ክልል ነው። በዋናነት ዛሬ በአሜሪካን የወያኔ አምባሳደር ሆኖ በተሾመው ካሳ ተክለብርሃን አስፈፃሚነት /በወቅቱ የክልሉ ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ እንደነበር ልብ ይሏል/ የምዕራብ ጎጃም ሥፋፊ የእርሻ መሬቶች በትግሬዎች አልያም ትግሬዎች ከብራዚል፣ ቻይና፣ ዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ ባስመጧቸው ሰዎች እንዲያዝ ተደርጓል። ይህ የትግሬ ወረራ እና መሬት ቅርምት ለከት ከማጣቱ የተነሳ ከራሳቸው አልፈው ገና የሀይስኩል ትምህርታቸውን እንኳን በአግባቡ ባልጨረሱ ልጆቻቸው ስም ሳይቀር የሚፈፀም መሆኑ ነው። ለዚህም ማሳያ የሚሆነን የስብሐት ነጋ ልጅ የሆነችው ህያብ ይህንን ከላይ የጠቀስነውን መሬት በወሰደችበት ወቅት /ትምህርቷን የጨረሰችው በ2015 መሆኑን ልብ ይሏል/ አሁን የዚህ ድርጅት ስራ አስኪያጅ ተብሎ ከተጠቀሰው ሐቂ ከሚባለው ወንድሟ ጋር በጣልያን ሀገር ፓድዋ በሚባል ስፍራ ትምህርቷን እየተማረች ነበር።

ነገሩን ይበልጥ የከፋ የሚያደርገው ደግሞ እነዚህ የትግሬ ተቀራማቾች እና ወራሪዎች በወሰዱት መሬት ላይ የአዋጭነት ጥናት፣ የአፈር ናሙና ጥናት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን ካስጠኑ በኋላ በቀጥታ ወደሥራ ከመግባት ይልቅ ትልቅ አቅም እና ዝና ያላቸው አለማቀፍ ድርጅቶችን በሽርክና ወደማስገባት እና ትልቁን ድርሻ በመሸጥ የእነሱን ምስል በትላልቆቹ ኮርፖሬሽኖች ጥላ የመሸፈን ስራ ነው የሚሰሩት። ይህንን የማሻሻጥ ተግባር ዕውን በማድረግ በኩል ሁለት የትግሬ ድርጅቶች በዋናነት የሚሰሩ ሲሆን አንደኛው ቢሮውን ሸራተን አዲስ ያደረገውና ቆስጠንጢኖስ በርሄ በሚባል ሰው የሚመራ ድርጅት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ መቀመጫውን ለንደን ያደረገውና ''አዲስ ካፒታል'' በመባል የሚታወቀው የኢያሱ በርሄ

/''ጋምቤላ አሎ በሎ'' እያለ የሚዘፍነው ሰው/ ልጅ በሆነው ረዊና ኢያሱ በርሄ ባለቤትነት የሚተዳደረው ድርጅት ነው።

ዛሬ የምዕራብ ጎጃም ምድር ምስጥ የበላው ዛፍ ሆኗል። ከላይ ሲታይ ያለ ይመስላል እንጂ በዚህ አይነት የትግሬ ወንጀል መሬቱ ከራሳቸው አልፎ የአለማቀፍ የመሬት ተቀራማቾች ሲሳይ ሆኗል። በእርግጥ ይህን ለአለማቀፍ ተቀራማቾች /Land Grabbers/ አሳልፎ የመሸጥ ተግባር የአማራ ተጋድሎ እያየለ መምጣት የውጪ ሰዎችን ፍሰት በመቀነሱ ሂደቱን በተወሰነ መልኩ እንዲጓተት አድርጎታል።

አማራዊው ወገናችን ሆይ! ከትግሬ ጋር የምንጋራው ሀገር እስካለን ድረስ እና ወያኔ ትግሬ በህይወት እስካለ ድረስ እንደህዝብ በመኖር ህልውናችን ላይ የሚደረገው ጥቃት ቢብስ እንጂ ለአፍታም ሊቆም እንደማይችል እሙን ነው። የአባቶቻችን አጽመ ርስት የሆኑ መሬቶቻችንን ከጎንደርና ላኮመልዛ /ከኦሮሞ ወረራ በኋላ ''ወሎ'' በሚል የሚጠራው ምድራችን/ በንጥቂያ በመውሰድ ትግሬን እንደ አንበጣ አስፍሮበታል። ይህም አልበቃ ብሎ በኢንቨስትመንት ሽፋን የተቀራመቱትን አማራዊ ምድራችንን ለአለማቀፍ ገበያ በግላጭ እያቀረቡ ነገሮቻችንን እያወሳሰቡት ይገኛል። ለዚህ ሁሉ ዘርፈ ብዙ ችግር ብቸኛው መፍትሔ የአማራ ብሔርተኝነትን በጽኑ ህዝባዊ መሠረት ላይ ማቆም፣ በአማራዊ ብሔርተኝነት ዙሪያ የነቃውንና የተሰባሰበውን ኃይልም ተጨባጭ ወደ ሆነ የትግል አቅጣጫ ማሰማራት የግድ ይላል። ወያኔ ትግሬም ይሁን የአገዛዙ መሠረት የሆነው የትግሬ ህዝብ ትንሽ የመተንፈሻ ጊዜ ካገኘ ከዚህም በላይ ሊያጠፉን የሚችልበት በርካታ ነገሮችን በጠረጴዛው ላይ እንዳስቀመጠ ከዚህ በፊት ''እሳት ተዳፈነ ማለት፥ ጠፋ ማለት አይደለም'' በሚል ርዕስ ባዘጋጀነው ጽሑፍ በተወሰነ መልኩ ለማየት ሞክረናል። ይህ እውነት ነው።ስለሆነም ወያኔ ትግሬ እስኪጠፋ እንዲሁም ከትግሬ ጋር የሚያገናኘን የመጨረሻው ክር እስኪበጠስ ድረስ የአማራ ህዝብ ትግል ለአይን ጥቅሻ ለምታክል ቅጽበት እንኳን ቢሆን ሊጓተት አልያም ሊቆም አይገባውም።

ደግሞም  በዙሪያችን ካለው ውስብስብ ከባቢያዊ የፖለቲካ ችግር አንፃር ብቸኛው መድህን ፤ ብሎም የመሸሸጊያ ከተማችን ጽንፈኛ አማራዊ ብሔርተኝነት ብቻ ነው!!!

ዴቭ ዳዊት።

የአማራ ብሔርተኝነት ይለምልም!     EPNP.INF

ኢሕብፓ

EPNP

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY